Keeping Children Safe
Setting tough international child safeguarding standards

+44 (0)20 7250 8325
www.keepingchildrensafe.global
CAN Mezzanine
49-51 East Road
London N1 6AH
United Kingdom

የህጻናት ደህንነት ጥበቃ ምንድነው?

የህጻናት ደህንነት ጥበቃ ማለት ለህጻናት ደህንነት በቀጥታ የሚሰሩ እና ከህፃናት ጋር የሚሰሩ ሀላፊነት ያለባቸው ድርጅቶች የስራ ባልደረቦቻቸ፤ የስራ ከንውኖቻቸው ና ፕሮገራሞቻቸው በህጻናት እና ላይ ምንም ጉዳት እንዳያደርሱ ማረጋገጥ ሲችሉ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ህጻናትበድርጅቶች ለሚፈፀምጉዳትም ሆነ ጥቃት እንዳይጋለጡና ድርጅቶችም በልጆች ደህንነት ላይ የሚያሳስባቸው ማንኛውም ጉዳይ ለሚመለከታቸው ባለ ሥልጣናት ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚያረጋግጥ ነው።

የህጻናት ደህንነት የሚጠብቁት እነማን ናቸው?

የህጻናት ደህንነት መጠበቅ (keeping children safe) ተልዕኮአችን በየትኛውም ቦታ የሚገኙ ልጆች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ነው ። በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ የህፃናት ደህንነት ጥበቃ ደረጃዎችን ለህጻናት በቀጥታ የሚሰሩ እና ከህፃናት ጋር የሚሰሩ ሁሉም ድርጅቶች አጠቃላይ የሆነ የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎች እንዲወስዱ አዘጋጅተንላቸዋል፡፡ እነዚሁ የደህንነት ጥበቃ ደረጃዎቻችን እና ምክሮቻችን በማንኛውም ሌላ ድርጅት ወይም መንግስት ተጽዕኖ የማይደረግባቸው መሆኑ የእኛን ገለልተኛ አካልነት ያሳያል፡፡

የመመሪያ መርሆዎች ምንድን ናቸው?

- ሁሉም ህጻናት ከጉዳት የመጠበቅ እኩል መብት አላቸው ፡፡
- ማንኛውም አካል የህጻናት ን የደህንነት ጥበቃ የመደገፍ ሃላፊነት አለበት ፡፡
- ድርጅቶች አብረዋቸው ለሚሠሩ፤ በስራ አጋጣሚም ሆነ ከዚያ ውጭ ለሚያገኟቸው ፤ ወይም በስራ ከንውኖቻቸው ምክንያት ተፅዕኖ ለሚደርስባቸው ህጻናት እንክብካቤ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡
- ድርጅቶች ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በአጋርነት የሚሰሩ ከሆነ አጋሮቻቸው የህጻናት ን ደህንነት በመጠበቅ ረገድ ዝቅተኛውን መስፈርት እንዲያሟሉ የመርዳት ኃላፊነት አለባቸው ፡፡
- በህጻናት ደህንነት ጥበቃ ዙሪያ የሚከናወኑ ሁሉም ተግባራት በዋናነት የህጻኑን ሁነኛ ፍላጎቶች የማከለ ከነዚህም ፍላጎቶች ጋር በጭራሽ የማይጣረስ ሊሆን ይገባል ፡፡

ደረጃዎቹ ምንድን ናቸው?

ደረጃ 1 ፖሊሲ - ድርጅቱ በህጻናት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል እና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ቁርጠኛ መሆኑን የሚገልጽ ፖሊሲ ያወጣል ፡፡ ፖሊሲው በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን (UNCRC) እንደተመለከተው ህጻናት ከጥቃት እና ብዝበዛ የመጠበቅ መብቶችን ያንፀባርቃል ፡፡

Keeping Children Safe is a trading name of KCS Coalition, a Company Limited by Guarantee registered in England and Wales.
Company number: 07419561. Charity registration number: 1142328.

- ፖሊሲው በድርጅቱ ሥራ አመራር አካል የፀደቀና በሁሉም የድርጅቱ ሠራተኞችና ተባባሪዎች ላይ የሚፈፀም ሊሆን ይገባል ፡፡

- ፖሊሲው በተገቢው ሁኔታ የታተመ፤ ለህዝብ በይፋ የሚታወቅና በስፋት የተሰራጨ መሆን አለበት ፡፡

- ሥራ አስኪያጆች የፖሊሲውን አፈፃፀም የመቆጣጠር ልዩ ኃላፊነት አለባቸው ፡፡

ደረጃ 2 ሰዎች - ድርጅቱ በሠራተኞቹና በተባባሪዎቹ ላይ ግልጽ ኃላፊነቶችንና ከእነርሱ የሚጠበቅባቸውን ጉዳዮች በግልፅ ያስቀምጣል፤ እንዲሁም ይኸንኑ ሠራተኞች እንዲረዱና ተጣጥመው በአግባቡ እንዲሠሩ ይደግፋቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የደህንነት ጥበቃን በተመለከተ ቁልፍ ሠራተኞች በተለያየ ደረጃ (የዳይሬክተር ደረጃን ጨምሮ) እንደ "ተጠሪ" ሆነው የሚሰሩ መሰየም ያለበት ሲሆን በግልጽ የተቀመጠ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ያላቸውም ሊሆኑ ይገባል፡ ፡

- የሰራተኞች ቅጥር ሂደት ጠንካራ የሆነ የህጻናት ደህንነት ጥበቃ ማረጋገጫ እርምጃዎች ያካተተ ሊሆን ይገባዋል፡፡

- አዋቂዎች በህጻናት ላይ እና ህጻናት በሌሎች ህጻናት ላይ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ ባህሪዎችን የሚያስገነዝቡ የጽሑፍ መመሪያዎች ሊኖሩ ይገባል ፡፡

- እነዚህም መመሪያዎች በህጻናት ደህንነት ጥበቃ ላይ አጋር አካላትን ፣ ማህበረሰቦችን እና ህጻናት ን ለማሳተፍ የሚያስችሉ መመሪያዎች ይሆናሉ ፡፡

ደረጃ 3 አሰራሮች - በመላው ድርጅቱ ተግባራዊ የሚደረግ የህጻናት ደህንነት ጥበቃ አሰራሮችን በማዘጋጀት ድርጅቱ ለህጻናት ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ይፈጥራል ፡፡ ድርጅቶች በሚሰሩባቸው አካባቢዎች ከሕግ ፣ ከማኅበራዊ ደኅንነትና ከህጻናት ደህንነት ጥበቃ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የሚሰጡ አካባቢያዊ ዳሰሳ ያከናውናሉ ፡፡

- የህጻናት ጥበቃ ሥጋት ዳሰሳዎች እና የማስተካከያ ስልቶች በድርጅቱ ሁሉም ደረጃዎች ባሉ ነባር የስጋት ዳሰሳ ሂደቶች ውስጥ የተካትተቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

- የህጻናት ደህንነት የመጠበቅ እርምጃዎች ካሉት ነባር ሂደቶችና ስርዓቶች ጋር ተዛምደው መከወን አለባቸው፡፡ እነዚህ ነባር ሂደቶች ለምሳሌ (ስትራቴጅካዊ ዕቅድ ፣ በጀት አመዳደብ ፣ ምልመላ ፣ የፕሮግራም ትግበራ ኡደት ፣ የስራ አፈፃፀም አመራር፣ የግዥ አፈፃፀም ፣ አጋር ስምምነቶችና አመራር ሥርዓቶች ወዘተ) ናቸው፡፡

- በህጻናት ደህንነት ጥበቃ ዙሪያ ሊከሰቱ የሚችሉ አጋጣሚዎች፣ አደጋዎችና አሳሳቢ ጉዳዮች ከየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ሪፖርት የማድረግና ምላሽ የመስጠት ሂደት ሊዘጋጅ ይገባል።

ደረጃ 4 ተጠያቂነት - ድርጅቱ የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎቹን ይከታተላል እንዲሁም ይገመግማል።

- የህጻናት ደህንነት ጥበቃ ፖሊሲዎችና አሰራሮች አተገባበር በየጊዜው ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል ፡፡
- ሥራው ያለበት ደረጃ ፣ አፈጻጸም እና ከተግባር የተገኙ ትምህርቶች ለቁልፍ ባለድርሻ አካላት ለምሳሌ የደርጅቱ የስራ አመራር መድረኮች እንደአስፈላጊነቱ ከድርጅቱ ውጪ ለሉ ወይም ለገለልተኛ አካላት ሪፖርት ሊደረግ እንዲሁም በድርጅቱ ዓመታዊ ሪፖርቶች ውስጥ ሊካተቱ ይገባል።
- በተጨባጭ ከተገኙ ልምዶች በመማር በህጻናት ደህንነት ጥበቃ እርምጃዎች ላይ የሚደረጉ የፖሊሲ ግምገማ እና ለውጦችን ማከናወን ይገባል ።
- በየሶስት አመቱ ፖሊሲዎችና አሰራሮች በውጭ ገምጋሚ አካል ወይም ኦዲተር በመደበኛነት ሊገመገሙ ይገባል፡፡